Arlington County Council PTA

everychild. onevoice.®

## በርቀት የመማር (“ቨርቹዋል ለርኒንግ”) ወቅት የግላዊነት (“ፕራይቬሲ”) አያያዝን የሚመለከት መግለጫ

ሴፐቴምበር 7፣ 2020

የዚህ ሰነድ ግብ፣ ተማሪዎች በርቀት መማርን በሚጀምሩበት ወቅት፣ ግላዊነትን (“ፕራይቨሲ”) አስመልክቶ በታሳቢነት መያዝ ስላለባቸው ሁኔታዎች ወላጆች  መረጃ እንዲኖራቸውና ንቃተ ህሊናቸው ከፍ እንዲል ለማድረግ ነው። ይህ ሰነድ የህግ ምክር ወይም ህጉ ይኸን ይመስላል ለማለት ታስቦ የተዘጋጀ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። በዚህ ጉዳይ ላይ ሙያዊ የህግ እርዳታ የምትፈልጉ ከሆነ እንደየራሳችሁ የግል ሁኔታ ሙያዊ የህግ ምክር ሊሰጣችሁ የሚችል የህግ ባለሞያን አነጋግሩ።

የአርሊንግተን ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከነበሩት የትምህርት ዓመታት ጨርሶ የማይመሳሰል፣ በቪዲዮ ካሜራዎች መገልገልን የሚያካትት የርቀት ትምህርትን (“ቨርችዋል ለርኒንግ”)፣ በለስለስጌ (“ሶፍትዌር”) መድረኮች አማካኝነት ሲጀምሩ ፣ የአርሊንግተን ካውንቲ “ፒቲኤ”ዎች (የወላጅና የአስተማሪ ማህበሮች) ምክር ቤት (ሲ ሲ ፒ ቲ ኤ) “ኤፒ ኤስ” (“አርሊንግተን ፐብሊክ ስኩልስ”) እና ወላጆች ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ወስጥ ጥራት ያለው አስተምህሮት ለልጆቹ እንዲሰጥ  ለማስቻል  ያሳዩትን ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በፍጥነት የመለማምድ ችሎታ እና  ዝዴኛነት ያደንቃል። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በፍጥነት መለማመድ ባርቆ አሳቢነት ካልታጀበ፣ የተማሪዎችን ትምህርት፣ ደህንነት፣ እና የላዊነት መረጃ በሚመለከት አሉታዊ የሆነ ተፅእኖ  ሊያደርጉ የሚችሉ ያልታሰቡ ወጤቶችን ሊያስከትል ይችላል።

ሲ ሲ ፒ ቲ ኤ ፣ በአንድ ላይና በአንድ ጊዜ በቀጥታ ስርጭት (“ላይቭ”) ፣ተማሪዎች በየቤታቸው እንዳሉ የሚሰጥ ሊሰራ የሚችል የመማር ሂደት መርሃ ግብር ለማቀነባበር በነበረው ሩጫ ምክንያት፣ ወላጆች፣ ተማሪዎች እና የ “ኤፒ ኤስ” ሰራተኞች ገና ያልተገንዘቡዋቸው (ያላሰቡባቸው) አዳዲስ ክስተቶች እንዴት ሊከተሉ እንደሚችሉ ውይይት እና ግምገማ ሲያደርግ ነበር። ሁላችንም፣ በሀገር አቀፍ ድረጃም ጭምር፣ የምንገኘው ገና ፍኖተ ካርታ ያልወጣለት ጉዳይ ላይ ነው። ማንኛችንም ስለነዚህ አዳዲስ ክስተቶች ትክክለኛውን መልስ ገና አላገኘንም። **ሲ ሲ ፒ ኤ በነዚህ ክስተቶች ላይ ከማህረሰቡ ጋር ተጨማሪ ውይይት ለማካሄድ እና ሁሉም ሰው እንዴት የርቀት ትምህርት አሠጣጡን ለተማሪዎቻችን የተሳካ ለማድረግ እንደሚቻል ያለው ግንዛቤ እኩል ደረጃ ላይ እንዲሆን የማድረግ ተስፋ ሰንቋል።**

ዋና ዋና ጭብጦች:

- ቪዲዮና ኦዲዮ ወደተማሪዎች ቤቶች ማስተላለፍን፣ የሚተላለፉትን ቪድዮና ኦዲዮዎች አቀዳድን፣ እንዲሁም ከነዚህ ቅጂዎች አያያዝና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ግላዊነትን የሚመለከቱ ስጋቶች (አሳሳቢ ሁኔታዎች) አሉ።
- አስተማሪዎች በልጆች ላይ ጥቃት ሲደረግ ካዩ ለህግ ማሳወቅ ግዴታ አለባቸው (“ማንዳቶሪ ሪፖርተርስ”) ። በርቀት ትምህርት አሰጣጥ ጊዜ በተማሪ ቪድዮ ወይም ኦዲዮ ላይ አስተማሪዎች ሊታዘቡዋቸው የሚችሉ የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ የቤተሰብ ሁኔታዎች ወይም ባህርይዎች ሊከሰቱ ይችላሉ።
- ስለምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ልዩነት እና የአኗኗር ሁኔታና እነዚህም ልዩነቶች፣ በቀጥታም ሆነ በቅጅ፣  በቪዲዮ ወይም አድዮ ስርጭት ወቅት፣ ሊታዩ እንደሚችሉ ትብ መሆን (“ሴንሲቲቪቲ”) የአርሊንግተን የህዝብ ት/ቤቶች ተማሪዎች የመማር ሂደትና ደህንነት ጋር የሚያያዝ የፍትህ ጉዳይ/ ጥያቄ ሁኖ ግንዛቤ ወስጥ መግባት አለበት።

በቅድሚያ ፣ ልጆች በየትምህርት ቀኑ ለሰዓታት በቪዲዮ ቀጥታ ስርጭት ራሳቸውን ማሳየታቸው፣ የስርጭቱን አላማ :- ማለትም ትምህርት መገብየት፣  ላይ ጣልቃ ሊገባ ይችላል።  የሚከተሉትን ጭምሮ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት፣ በርካታ ምክንያቶች አሉ:

- ካሜራ ፊት የመሆን ዓይን አፋርነት፣
- ክበስተጅርባ የሚታየው የተማሪው መኖሪያ ቤት ድባብ ስለተማሪው የአኗኗር ሁኔታ ስለሚያስተላልፈው መልዕክት መጨነቅ፣
- ሌሎች ተማሪዎች በካሜራዎቻቸው አማካኘት ስለሚሳዩአቸው ነገሮች አሉታዊ ማወዳደሮች፣
- አንድ ልጅ ሊቆጣጥረው የማይችለው፣ ነገር ግን ሊያዋርደው/ሊያሳፍረው የሚችል ሆን ተብሎ ሳይሆን የሚፈፀም ድርጊት ይፈጠራል ብሎ የመፍራት፣

- ተማሪው ሳያውቀው ቤተሰቡን ሊያሳፍር የሚችል ነገር ( ህገ ወጥ ሆነም አልሆነ) በማጋለጡ አፀፋዊ ቅጣት ሊደርስብት የሚችል መሆኑ፣
- ዘለግ ላለ ጊዜ ከሌሎች አንሶ ላለመታየት የሚደረገው ጥረት የሚያስከተለው ጭንቀት።

ከኤፒ ኤስ ቁጥጥር ወጭ በሆኑ በርካታ ምክንያቶች ተማሪዎች በሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነት ላይ ሊያተኩሩ አይችሉ **ይሆናል። ቢሆንም ግን የተማሪዎች በቪዲዮ ቀጥታ ስርጭት መሳተፍ፣ መደበኛው ("ዲፎልት") የክፍል ትምህርት አሰጣጥ የመሆኑን ወይም ያለመሆኑን ውሳኔ የመስጠቱ ጉዳይ ኤፒ ኤስ እጅ (ቁጥጥር ስር) ነው።** በበኩላችን፣ የ ኤፒ ኤስ አስተዳዳሪዎች የቪዲዮ ካሜራ ሳያበሩ በርቀት ትምህርት ለመሳተፍ የሚያስችሉ ምን ምን አማራጮች እንዳሉና አማራጮቹ ሊኖሯቸው የሚችሉትን ጉዳቶችና ጥቅሞች በግልፅ ለወላጆችና ለተማሪዎች እንዲያስረዱ እናበረታታቸዋለን። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አሉታዊ ተፅእኖዎች መካከል አንዳንዶቹ (ለምሳሌ- የራስ/የብቻ የሆኑ ክፍሎች እጥረት፣ ወይም በካሜራ አማካይነት ስልሚተላላፈው ትምህርት በራስ መተማመን እንዲኖራቸው የሚያግዙ መርጃዎች ('ሪሶርስስ")) ከሚገባው በላይ ባልተመጣጠነ ሁኔታ አነስተኛ የገቢ ምንጭ ያላቸው ቤተሰቦች ላይ ሊድርሱ እንደሚችሉ በተለይ ያሰብንበት ጉዳይ ነው። **የርቀት ትምህርት በሚሰጥበት ሰዓት፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛውን ጥንቃቄ የማድረግ ተሞክሮ ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርግ የትምህርት አሰጣጥ የ "ኤ ፒ ኤስ" ተማሪዎችን ብቃት ያለው አያገልግሎት አይሰጣቸውም።**

እንዲሁም የ"ኤ ፒ ኤስ" መመሪያ፣ ባንዳንድ ሁኔታዎች ፣ የተማሪዎች የቀጥታ የቪዲዮ ስርጭቶችን በመኖሪያ ቤት ወስጥ መቅዳትን ማበራታታቱና ባጠቃላይም መፍቀዱ አሳስቦናል። "ሲ ሲ ፒ ቲ ኤ" አስተማሪዎችን መቅዳት ጥቅም እንዳለው ይገነዘባል፡- እንዳስፈላጊነቱ የተሰጠውን ትምህርት መድገም ይቻላል እና ት/ቤቱም፣ ድንገት ለህግ ተጠያቂነት ምክንያት ቢኖር፣ ከተማሪ ጋር በሚደረግ ያንድ ለአንድ መስተጋብሮች የአስተማሪውን/ዋን አኳኋዋን ("ኮንዳክት") የሚያመለክት የቅጂ መዝገብ ይኖረዋል።

ተማሪዎችን በቤታቸው በመቅዳት የሚገኘው ጥቅም ግልፅነቱ አነስተኛ ነው። እንዲያውም ብዙ ጉዳት አለው። በተለይ እኩዮች የትምህርት ዓመቱን ሙሉ የርስ በራሳቸውን ቅጅዎች ሊያገኙ በሚችሉበት ሁኔታ፣ የማናቸውንም ዓይነት የአካዴሚያዊ ስህተት ወይም አሳፋሪ ("ኤምባራሲንግ") አኳኋንን እይታ ያገዝፋል። በተጭማሪም፣ "ኤ ፒ ኤስ"፣ ዕርቃን መሆንን (ተማሪው፣ ሌላ ልጅ፣ ዐዋቂ ሰው) ፣ በግል ሰውን መለየት የሚያስችሉ መረጃዎችን፣ በሌሎች በትምህርቱ ተሳታፊ ባልሆኑ የቤተሰብ አባላት መካከል የሚካሄዱ መስተጋብሮችን እና ሌሎች በርካታና አንድ ግለሰብ በቤቱ ወስጥ እንዲኖር የሚጠብቀው ግላዊነትን ጭምሮ፣ በተማሪዎች ቤት ወስጥ ቅጂ በሚካሄድበት ውቅት ካሜራው ምን እንደሚቀዳ ለመቆጣጠር አይችልም።

"ኤ ፒ ኤስ"፣ በህግ አግባብ፣ በወላጆች ጥያቄ መሰረት፣ ወይም ወላጆች በሚለያዩበት ጊዜ፣ ልጆች ማንኛው ወላጅ ዘንድ እንድሚሆኑ ለመወሰን በሚደረግ ወይም በሌላ ህግ ንክ ክርክር፣ በመረጃ የማግኘት ህጋዊ መብት ("ኤፍ ኦ አይ ኤ") መሰረት የሚቀርብ ጥያቄን፣ ወይም፣ የፌዴራል መንግስት የስደተኞች ጉዳይ አስከባሪዎችን ጨምሮ፣ ከህግ አስከባሪዎች መጥሪያ ወይም "ዋራንት" ሲደርሰው ምን ማድረገ እንዳለበት የሚግልጽ መመሪያና በመሪያው መሰረትም ለመፈፀም የሚያስችለው ሰራተኞች አሉት ውይስ የሉትም የሚለው ጉዳይም ያሳስበናል። ወደ ሁዋላ ላይ ከትምህርት ውጭ ለሆነ ዓላማ ክንውን የሚጠይቁና፣ በአንዳንድ ሁኔታዎችም፣ ለህግ አስከባሪዎች መሰጠት የሚኖርባቸው በተማሪዎች ምኖሪያ ቤት ወስጥ የሚድረጉ የቪድዮ እና አዲዮ ቅጅዎችን የመሰብሰብ አስፈላጊነት ምክንያታዊነቱ እንዲገባን እንፈልጋለን። የሃብት እጥረት ባለበት ጊዜ "ኤ ፒ ኤስ" የሚያከናውናቸው ተግባራት የሰው ሃይልን ከተማሪዎች ትምህርትና ደህንነት ውጭ በሆኑ ተግባራት ላይ ያስርብኝ ይሆን የሚለውን እሳቤው ወስጥ ማስገባት አለበት።

"ኤ ፒ ኤስ"፣ ሌሎች ተማሪዎች በ "ኤ ፒ ኤስ" ልስለስጌ ('ሶፍትዌር") መድረከ በመገልገል እርስ በርሳቸው ሊቀዳዱ የሚችሉበትን ሁኔታ እማይቻል አድርጎባቸው እንደሆንም ይበልጥ መስማት እንፈልጋለን። "ኤ ፒ ኤስ" ፣ ራስ ቤት ውስጥ (ማንኛውም ሰው ቢሆን ግላዊነት አለኝ ብሎ በሚጠብቅብት) ፣ ከተወያዮቹ አንዳቸውም ለመቀዳት ፈቃዳቸውን ሳይሰጡ፣ የሚደረጉ ውይይቶችን የቨርጂኒያ ቅጂ ነክ ወንጀሎች እንዴት ሊመለከቷቸው እንዳሚችሉ ለተማሪዎች እንዲያሳውቅ እንፈልጋለን። ዕቅመ አዳም/ሔዋን ያላደረሰ/ች ልጅ፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላትንም ጨምሮ ፣ ለእንዲህ ዓይነቱ ቅጂ ፈቃዳቸውን መሰጠት ይችሉ እንደሆን እንዲብራራልን እንፈልጋለን።

በመጨረሻም የሚያሳስበን፣ ት/ቤቶች ህጋዊ ተግባር እያከናውኑ ቢሆንም በግዛቱ ("ስቴት") ህግ መሰረት ህጋዊ ("ፎርማል") ሂደቶችን የሚቀስቀስ ውጤት ሊያመጣ ስለመቻሉ ወላጆች አልተዘጋጁ ይሆናል የሚል ስጋት አለን። **በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን ዲሲፕሊን የሚያደርጉበት ዘዴ የልጆች ጥቃትን ወይም ችላ ማለትን በሚመለክት ጥርጣሬ ካላቸው ይኽንንው ለ"ቻይልድ ፕሮቴክሽን ሰርቪስስ" የማሳውቅ ገዴታ በተጣለባቸው ስዎች ፊት ማሳየት አልለመዱም። የቨርጂኒያ "ዲፓርትሜንት ኦፍ ሶሻል**

**ሰርቪስስ" እንኳን በህጋዊ አካላዊ ቅጣት እና ህጋዊ ባልሆነው የልጆች ጥቃት መካከል ያለው ልዩነት አጠያያቂ ሊሆን እንድሚችል ያምናል።** ከዚያም በላይ ዘርን እና ማህበራዊ መደብን አስመልክቶ በግልጽ የማይታይ አድልዎ ወይም ወገንተኘነት እንዳለ የሚያሳይ በርከት ያለ ምርምር አለ። ይኽም የዲሲፕሊን ግምገማዎችን ይበልጥ የተወሳሰቡ ያደርጋል።

በተጨማሪም፣ የግዛቱ ("ስቴት") ህግ፣ የትምህርት ቀጣናዎች ("ስኩል ዲስትሪክትስ") ፣አንድ ተማሪ ሌላ ሰውን ወይም ራሱን(ዋ)ን የመጉዳት ፍላጎትን ማሳየትን ጨምሮ፣ ይደርሱ ይሆናል ተብለው ይሚገመቱ አደገኛ ሁናቴዎችን ለመገምገም እንዲቻል የአደጋ ግምገማ ቡድኖችን የሚመለከት ፖሊሲ እንዲያዘጋጁ ያዛል። ውላጆች በወንድም እና/ወይም እህትማማቾች መካከል እቤት ውስጥ የሚደረግ፣ ነገር ግን ሌሎች ላይ የተቃጣ ቢሆን ወይም የተፈጸመው ከቤት ወጭ ቢሆን፣ የማይታለፍ መስተጋብርን ("ኮሙኒኬሽን") የተላመዱት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም መስተጋብሩ በርግጥ ጉዳት የማድረግ ፍላጎት የማያካትት መሆኑን ወላጆቹ ያውቃሉ። ይሁንና፤ ውንድምና/ወይም እህትማማቾች በርቀት ትምህርት ወቅት እቤት እያሉ እና አስተማሪም እየታዘባቸው/ እየታዘበቻቸው እርስ በርሳቸው ዛቻ ቢለዋውጡ ወይም ቢደባደቡ፤ አስተርማሪው(ዋ) ሁኔታው በቀጣይ እንዲገመገም የአደጋ ግምገማ ቡድን ማሳተፍ ሊያስፍለገው(ጋት) ይችላል።

በመሰረቱ ፣ ድርጊቱ ህጋዊ ቢሆንም እንኳ፣ አስተማሪ ስለታዘበው ብቻ፣ ምናልባት ህጋዊ ያልሆነ ድርጊት ወይም የአደጋ ምልክት ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ጣልቃ መግባትን የሚጥይቀ መሆኑ ብዙ ወላጆችን አግራሞት ላይ ሊጥላቸው ይችላል። አንዳንድ ዓይነት ህጋዊ የዲሲፕሊን እርምጃዎች ወይም የወንድም እና/ወይም እህትማማቾች ፀብ የህግ ጣልቃ ገብነት ሊያስከትል እንደሚችል ወላጆች የተሻለ መረዳት እንዲኖራቸው እና ከመላ የተማሪው ቤተሰብ አባላትም ጋር ስለ እነዚህ ጣልቃ ገብነት ስለሚያስከትሉ ድርጊቶች ውይይት እንዲያካሂዱ 'ሲ ሲ ፒ ቲ ኤ" ወላጆችን ያበረታታል። አንድ ቤተሰብ ግላዊነትን ለመግዛት አቅሙ ስላለው አንዳንድ የጥቃት ድርጊቶች ላይታዩ እንደሚችሉና ብሌላ በኩል ደግሞ ሊሎች ቤተሰቦች ግላዊነት ለመግዛት ስለማይችሉ ጥቃት ያልሆኑ ድርጊቶች እንኳን ቢታዩ ህግ ነክ የምርመራ ጥያቄዎች ሊካሄድባቸው እንደሚችል "ሲ ሲ ፒ ቲ ኤ" ልብ ይላል።

"ኤ ፒ ኤስ" ተማሪዎቹ መካከል ፍትህን ማዳበርና ተማሪዎችን ለህግ አስከባሪዎች አሳልፎ መስጠትን መቀነስ ላይ ባትኮረበት ባሁኑ ሰዓት፣ የ "ኤ ፒ ኤስ" ቤተሰቦች ቤቶቻቸው ላላስፈላጊ (ትእዛዝ ያለውጣባቸው) ፍተሻዎች እና ቅጂዎች ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ሳይታውቀው እያስገደዳቸው ሊሆን ይችላል። እነዚህ የቀጥታ ስርጭቶች እና ቅጂዎች ተማሪዎቹን ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የቤተሰብ አባላትና በቤቱ ወሰጥ የሚገኙ ሶስተኛ ወገኖች ለበርካታ አሉታዊ ሁኔታዎች እንዲጋለጡ ለማድረግ ይችላሉ። ለተማሪ ልጃቸው የግል / የብቻ ክፍል የመስጠት ችሎታ ላላቸው ቤተሰቦች እንዲህ አይነቱ ስጋት ውሱን መሆኑ የታወቀ ነው። ነገር ግን፣ ሌሎች ተማሪዎች ወይም የቤተሰብ አባላት ሊታዩና ሊቀዱ በሚችሉበት አንድ የጋራ ክፍል ወሰጥ ትምህርት የሚከታተሉ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች የጣልቃ ገብነቱ ድረጃ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል።

የ "ኤ ፒ ኤስ" ቤተሰቦችን መኖሪያ ቤት መከታተል ለርቀት ትምህርቱ የታለመለት ዓላማ አለመሆኑን ስለምንተማመን፣ "ኤ ፒ ኤስ"፣ ሊደርስ ስለሚችል ይኽን ዓይነት ችግር ቤተሰቦችን እንዲመክር እና እንዲህ ዓይነት ጣልቃ ገብነት እንዳይከሰት የሚያስችል መላ እንዲፈልግ በእጅጉ እናበረታታለን።

ሲ ፒ ቲ ኤ"፣ የ "ኤ ፒ ሲ" ማህበረሰብን በቀጣይ ከዚህ በላይ ስለተወሱት ጉዳዮች እንድምታና በሩቅ ትምህርት ምክንያት በተማሪዎች ትምህርትና ድህንነት ላይ የሚከሰቱ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ ምን ዓይነት አካሄድ መከተል እንዳለበት ዘዴ ለመዘየድ የላቀ ማብራሪያ እና ውይይት ውስጥ ለማሳተፍ ተስፋ ያደርጋል።

የ "ሲ ፒ ቲ ኤ" ሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ

ኤሚሊ ቪንሰንት፣ ፕሬዚደንት
ሜሪ ካዴራ፣ ም/ፕሬዚደንት
ክሌር ኖአኬስ፣ የፖሊሲ ም/ፕሬዚደንት
ካትሪን ኖቬሎ፣ የልዩ ፕሮጀክቶች ም/ፕሬዚደንት
ማይክ ኦ ሊሪ፣ ፀሐፊ
ኬንድራ አንደርሶን፣ ግንዘብ ያዥ